# መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ -መኢሶን-

# ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)

"NEW ETHIOPIA" P.O.BOX 5877 16305 SPANGA SWEDEN


የካቲት 27.1982

## መግለጫ

መንግስቱ ሃይለማርያም በየካቲት 26.1982 ለፓርቲው አስቸኳይ ስብሰባ ባደረገው ንግግር፣ የፓርቲው የፖለቲካ ቢሮ አንዳንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች እንዲለወጡ ሃሳብ ያቀረበ መሆኑን ገልጿል፡፡ እንዳለውም ከሆነ፣ 'የፓርቲው ስም እንዲቀየር፣ ፓርቲው ይበልጥ ተወካይነት እንዲኖረው፣ ተቃዋሚ ሃይሎች በፓርቲው ጥላ ሥር ሆነው በሃገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ እንዲሳተፉ' የሚሉት የፖለቲካ ፖሊሲ ዕቅዶችና ባጠቃላይ 'ቅይጥ ኢኮኖሚ' የሚባለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

መንግስቱ ሃይለማርያም አሁን ደግሞ በእንደዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ዘይቤ ለመወናኘት የተነሳሳው በንግግሩ እንዳለው፣ 'ኢትዮጵያ በዓለም—አቀፍ ደረጃና በተለይም በምስራቅ አውሮፓ ከሚከናወኑት ለውጦች ተነጥላ እንዳትቀር' በመጠነቁ ምክንያት ነው ብሎ **መኢሶን** አያምንም፡፡ እስከዚህም ድረስ እንዲሄድ ያስገደዱት ምክንያቶች የኢትዮጵያ ህዝቦች ለሰላምና ለዲሞክራሲ የሚያካሂዷቸው የተለያዩ ገልፅና ስውር ትግሎች ናቸው፡፡ እነዚህም፣ ጠቅላላው ፀረ—መንግስቱ አገዛዝ አቅዋምና ተቃውሞ፣ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተከታታይ የደረሱበት ውጥረቶች —የግንቦት 8.1981 የሠራዊት እንቅስቃሴና የሠራዊቱ ውስጥ ሁኔታ፣ የተለያዩት ግንባሮች የሚያካሂዷቸው ጦርነቶችና ወታደራዊ ድሎቻቸው፣ የተለያዩት የፖለቲካ ድርጅቶችና ማህበራዊ ሃይሎች የሚያካሂዷቸው ያላሰለሱ የፖለቲካና የማህበራዊ ትግሎች ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ "እኛም እንደሶሻሊስት አገሮች" በማለት በመንግስቱ የተሰጠው ምክንያት የዓለምን ህዝብ ለማታለልና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘበትን የፖለቲካ ከስረትና ብቸኝነት ለመሸፈን ነው፡፡

ይህ በዚህ ቢሆን፣ **መኢሶን** በተጨማሪ አሁን በመንግስቱ ሃይለማርያም የቀረቡትን ሃሳቦች በቂና አጥጋቢ ናቸው ብሎ የማይቀበላቸው መሆኑን ያሳውቃል፡፡ የመንግስቱ አገዛዝ ከስረ—መሠረቱ መለወጥ ያለበት አገዛዝ እንደሆነ፣ የ**መኢሶን** እምነት ነው፡፡ የፓርቲው ስም ተቀየረ / አልተቀየረ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች ለተሳትፍ ተጠሩ / አልተጠሩ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች በይፋ እንደሚረጋገጡ እንደም የተነገረ ነገር የለም፡፡

ባጭሩ፣ አገራችን እንዲህ በከፍተኛ ስቃይና ውጥረት ውስጥ በምትገኝበት ወቅት፣ መንግስቱ ሃይለማርያም ለአገሪቱ መሠረታዊ ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉትን ጉዳዮች ጠርሰ አላነሳቸውም፡፡ በዛሬው ወቅት የኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ ቁልፍ መፍትሄዎች የሰላምና የዲሞክ

ራቢ ጥያቄ ናቸው። የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላም ካገኙና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ከተጎናፀፉ ረሃብን ለማጥፋት፣ ያኗኗራቸውን ዘዴ ለመወሰን፣ የሚፈልጉትን ዓይነት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመምረጥ ይችላሉ። በሰላምና ዲሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ መንግስቱ ሃይለማርያም የፓርቲውን ስም ቀየረ / አልቀየረ፣ ኢኮኖሚውን ቀየጠ / አልቀየጠ አገሪቱ ከምትገኝበት የፖለቲካ ጭቀና፣ የኢኮኖሚ ውድቀትና የጦርነት አዘቅት ልትላቀቅ አትችልም።

ስለሆነም፣ መኢሶን፣ መንግስቱ ለማገገም በማለት የወረወራቸውን ሃሳቦች የማይቀበለውን ያህል፣ መንግስቱ ሃሳቦቹን ያቀረበው በፖለቲካ ጥያቄዎች ጭምር ላይ እንዲያፈገፍግ ስለ ተገደደ መሆኑን ይረዳል። በዚህም ሁኔታ፣ ተቃዋሚ ሃይሎች ሁሉ በአንድ ብሄራዊ የሰላምና የዲሞክራሲ መድረክ ላይ ተሰባስበውና ተባብረው መታገላቸውና የጋራ ግፊት ለማድረግ መተባበራቸው አጅግ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም፣ መኢሶን በዚህ አጋጣሚ፣ የኤርትራ ግንባሮችን ጨምሮ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ በአንድ ብሄራዊ የሰላምና የዲሞክራሲ መድረክ ላይ በአንድነት ተሰብስበን እንድንታገል ጥሪውን ያቀርባል። ስለሽግግር ዘመን ያወጣውን ፕሮግራም አስመልክቶ በጥር 17.1982 ለድርጅቶች ሁሉ የላከውንም ደብዳቤ በማደስ፣ አስቸኳይ ግኑኝነቶችና ውይይቶች እንዲደረጉ በድጋሚ ይጠይቃል። መኢሶን በኢትዮጵያ ምድር ሰላምና ዲሞክራሲ እንዲሰፍኑ ለማድረግ በሚደረገው ትግል ውስጥ፣ ማናቸውንም ገንቢ አስተዋፅኦ ለማድረግ ዝግጁ ነው።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ